በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት የስራ ሂደት

የንግድ ምልክትን ለመመዝገብ የወጣ ተጨማሪ መመሪያ

**641/2013**

ታህሳስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የንግድ ምልክት ምዝገባን አስመልክቶ የተዘጋጀ መመሪያ

በሃገራችን የተጠናከረ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አሰራር መኖር ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን በማስፈን የንግዱ ማህበረሰብ መልካም ስምና ዝናውን ጠብቆ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን ከማስቻሉም በላይ በህገወጥ መንገድ በገበያ ላይ መሳከርን በመፍጠር ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የሚፈልጉትን አካላት በማዳከም የሸማቾችን ጥቅም የማስጠበቅና የውጭ ኢንቨትመንትን በመሳብ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን የሚያስችል ስርዓት ነው፡፡

ይህንን ዓላማ ለማሳካት ያስችል ዘንድ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 የወጣ ሲሆን አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስችል ማስፈጸሚያ ደንብ 273/2005 በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ተግባራዊ በመሆኑ አዋጁንና ይህን ደንብ መሰረት በማድረግ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተመዘገቡ ሁሉንም የንግድ ምልክቶች እንደገና መመዝገብ የግድ የሚል በመሆኑ፤

አዋጁ ከወጣ በኋላ የተመዘገቡ የንግድ ምልክቶችንም ቢሆን በአዋጁ በተቀመጠው ጊዜና በደንቡ የተመላከቱ ጉዳዮችን ያካተተ የምዝገባ ሰርተፊኬት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በደንቡ አንቀጽ 59 መሰረት ጽ/ቤቱ ማስፈጸሚያ መመሪያ ለማውጣት በተሰጠው ስልጣን መሰረት የንግድ ምልክት ምዝገባ የሚመራበትን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ አዘጋጅቶ የንግድ ምልክት እንደገና ምዝገባ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ሆኖም በዚህ የምዝገባ ሂደት የታዩ ግልጽነት የጎደላቸው ጉዳዮችን በማስተካከል የንግድ ምልክት ዝገባንና የምዝገባ ማስተካከያ ስራዎችን በአጭር ጊዜ ማከናወን እንዲቻል ይህ ተጨማሪ የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ድንጋጌ

1) አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የንግድ ምልክትን ለመመዝገብ የወጣ ተጨማሪ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) ትርጓሜ

ቀደም ሲል የንግድ ምልክትን እንደገና ለመመዝገብ በወጣው የመጀመሪያ መመሪያ ላይ የተጠቀሱት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣

1) አዋጅ" ማለት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 ማለት ነው

2) ቀደም ሲል የነበረው የጥበቃ ጊዜ ማለት፡- የንግድ ምልክት እንደገና ምዝገባ ከመካሄዱ በፊት በጽ/ቤቱ ለሃገር ውስጥ አመልካቾች ለሁለት ዓመትና ለውጭ ሃገር አመልካቾች ለስድስት ዓመት ይሰጥ የነበረው የንግድ ምልክት የጥበቃ ጊዜ ማለት ነው፡፡

3) መሰረታዊ ችግር ያለበት የንግድ ምልክት ማለት፡- የንግድ ምልክት አዋጁ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የተመዘገቡ የንግድ ምልክቶችን የሚመለከት ሲሆን ጉድለቱም በአዋጁ አንቀጽ 6 እና7 ላይ የተመለከቱትን በንግድ ምልክቱ ላይ የሚታይ መሰረታዊ ግድፈትን የሚመለከት ይሆናል፤

4) በማህበረሰብ ግብይት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ማለት፡- ለህብረተሰቡ ጥቅም ሲባል የተለያዩ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ በግብይት ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶችን ይመለከታል፡፡

5) የጥበቃ ጊዜ ማለት፡- በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጁ የተጠቀሰውን የ 7ዓመት የጥበቃ ጊዜ የሚመለከት ሲሆን ይሄውም የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

3) ከንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ጋር ተያይዘው መቅረብ ስላለባቸው ሰነዶች፤

1) የንግድ ምልክትን ለማስመዝገብ የሚቀርቡ የሃገር ውስጥ አመልካቾች ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን የውጭ ሃገር አመልካቾች ደግሞ በየሀገራቸው ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ የተረጋገጠ የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የንግድ ምልክት ምዝገባ ሰርተፊኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

2) ከላይ የተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሃገር ውስጥ አመልካቾች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዳወጡ ከንግድ ምልክት ጋር ተያያዥ የሆኑ ስራዎችን መስራት እንዲያስችላቸው የንግድ ስራ ፈቃድ ከማውጣታቸው በፊት በኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም በንግድ ምዝገባ ፈቃድ የንግድ ምልክት ማመልከቻ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን የንግድ ምልክት ምዝገባው በሚካሄድበት ጊዜ ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃዳቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

3) ከላይ በተራቁጥር 3.1 የተጠቀሰው ቢኖርም የውጭ ሃገር አመላካቾች በሀገራቸው የንግድ ስራ ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነና ድርጅቶች ወደ ንግድ ስራ ውስጥ የሚገቡት በንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፤ ወይም በሰርተፊኬት ኦፍ ኢንኮርፖሬሽን ከሆነ ይህንን የሚያረጋግጥ ሰነድ በአመልካቹ ከቀረበ ይሄው ሰነድ ተቀባይነት ይኖረዋል። ሆኖም የተሳሳተ ሰነድ ያቀረበ አካል ከተገኘ የምዝገባ ሂደቱ ፈራሽ ይደረጋል። እንደአስፈላጊነቱም በሃገሪቱ ህግ መሰረት ተጠያቂም ይሆናል።

4) ከላይ በተራቁጥር 3.1 እንደተገለጸው የውጭ ሃገር አመልካቾች በውጭ ሃገር የንግድ ምልክቱ የተመዘገበበትን ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ እንደለባቸው የተገለጸ ሲሆን ይሄው ሰነድ ከየትኛውም የውጭ ሃገር ተረጋግጦ ሊቀርብ ይችላል።

4) <u>በማህበረሰብ ግብይት</u> <u>ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ንግድ ምልክት ጥበቃን በተመለከተ፤</u>

በማህበረሰብ ግብይት ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች ከሚመለከተው አካል ወደ ስራ እንዲገቡ የተሰጣቸውን <u>የስራ ፈቃድ</u> በማቅረብ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ።

5) ከውጪ ሀገር ስለሚቀርቡ ሰነዶች፤

የንግድ ምልክትን ለማስመዝገብ ከውጭ ሃገር የሚቀርቡ የውክልና ማስረጃ፤ ሰነዶች በሃገሪቱ ህግ መሰረት በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በኩል ተረጋግጦ መቅረብ ያለበት ሲሆን የንግድ ምልክት ፈቃድ ውልና መብት ማስተላፍን የተመለከቱ የስምምነት ሰነዶች ስምምነቱ በተፈጸመበት ሃገር በሚገኙ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ተረጋግጦ መቅረብ አለበት ።

6) የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ስለሚወጣበት ቋንቋ፤

1) የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ሰፊ ሃገራዊ ስርጭት ባለው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በጽ/ቤቱ እየተዘጋጀ በአማርኛ መውጣት አለበት፤

2) ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ቢኖርም ተቃውሞ ጥሪውን በተጨማሪ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲወጣላቸው አመልካቾች ከጠየቁ ጽ/ቤቱ በአማርኛ ከተዘጋጀው ማስታዎቂያ ጋር አንድ ዓይነት የሆነ ማስታዎቂያ በዚሁ ቋንቋ አዘጋጅቶ እንዲታተም ለአመልካቹ ይሰጣል።

7) ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የትርጉም ስራዎችን በተመለከተ፤

በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ያልተዘጋጀ ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ተተርጉሞና ከዋናው ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ በሚኖርበት ጊዜ በሃገር ውስጥ ወይም በውጭ ሃገራት ይህንን ስራ እንዲሰሩ ፍቃድ በተሰጣቸው የትርጉም ቤቶች በኩል ተተርጉሞ መቅረብ ይኖርበታል።

8) ቀደም ሲል በነበረው አሰራር በአስመጪነት የንግድ ስራ ፈቃድ ንግድ ምልክት አስመስዝግበው በንግድ ስራ ላይ ስለተሰማሩ ባለመብቶች፤

አዋጁ ከወጣ በኋላ በአስመጪነት የንግድ ስራ ፈቃድ ለምርቶች ንግድ ምልክት አስመዝግበው በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ምርቱን ለማምረት የሚያስችል ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ ካቀረቡ ንግድ ምልክቱን በቅድሚያ የማስመዝገብ መብት ያገኛሉ።

9) ከንግድ ምልክት የጥበቃ ጊዜ ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ጉዳዮች፤

1) አዋጁ ከወጣ በኋላ የተመዘገቡና የንግድ ምልክት እንደገና ምዝገባው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የሰባት ዓመት የጥበቃ ጊዜያቸው የተጠናቀቁና የሚጠናቀቅ የንግድ ምልክቶች ዕድሳት ብቻ በማድረግ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማስተካያ ያካሄዳሉ። ስለሆነም እራሱን የቻለ የምዝገባ ማስተካከያ እንዲያካሂዱ አይገደዱም፤

2) አዋጁ ከወጣ በኋላ የተመዘገቡና የጥበቃ ጊዜያቸው ያልተጠናቀቀ የንግድ ምልክቶች ቀደም ሲል በወጣው መመሪያ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምዝገባ ማስተካያ ማካሄድ ይኖርባቸዋል። ሆኖም ቀደም ሲል የነበረው የጥበቃ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ለንግድ ምልክት ዕድሳት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በቅድሚያ የምዝገባ ማስተካያ ማካሄድ ይኖርባቸዋል።

10) <u>የጽ/ቤቱ ውሳኔ ለባለጉዳዩ እንደደረሰው የሚቆጠርበት ጊዜ</u>፤

ከንግድ ምልክት ምዝገባ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማመልከቻዎች ለጽ/ቤቱ ሲቀርቡና ጽ/ቤቱ ተገቢውን ምላሽ በጽሁፍ መስጠት ሲኖርበት ምላሹ ለአመልካቹ እንደደረሰው የሚቆጠረው የተጻፈው ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል። ደብዳው ወጪ መሆኑን ለአመልካቹ ማስወቅ የሚቻልበትን ሁኔታ ጽ/ቤቱ ያመቻቻል።

11) <u>በአንድ ማመልከቻ ውስጥ ስለሚቀርቡ ተከታታይነት ያላቸው ንግድ ምልክቶች ብዛት ስለመወሰን</u>፤

ተከታታይነት ስላላቸው የንግድ ምልክት ምዝገባ በደንቡ አንቀጽ 49 የተገለጸ ቢሆንም በአንድ ማመልከቻ ላይ መቅረብ ስለሚችሉ ተከታታይ የንግድ ምልክቶች ብዛት የተደነገገ ባለመሆኑ በአንድ ማመልከቻ ላይ የሚቀርቡ ተከታታይ የንግድ ምልክቶች ብዛት ከ5 መብለጥ አይኖርባቸውም።

12) <u>የቦታ ስያሜዎችን በተመለከተ</u>

1) አንድ የንግድ ምልክት አመልካች ድርጅቱ የሚገኝበትን ወይም ንግድ ምልክቱ የሚወክለው ምርት የሚመረትበትን ሃገር ወይም ከተማ ስያሜ ከሌላ ሊመዘገብ ከሚችል የንግድ ምልክት ጋር አያይዞ ማስመዝገብ ይችላል። ሆኖም በእነዚህ ስያሜዎች ላይ የብቸኝነት መብት አያሰጠውም።

2) በሃገራችን የሚገኙ የክልል፣ የዞንና የወረዳ ዋና ከተሞችን፣ በንግድ ምልክትነት መጠቀም የማይቻል ሲሆን ንግድ ምልክቱ የሚወክለው ምርት ወይም አገልግሎት በባህሪው ወይም በጥራቱ

ምርቱ ከሚገኝበት አካባቢ ጋር የተቆራኘ ከሆነ ማንኛውንም የአካባቢ ስያሜ በንግድ ምልክትነት መጠቀም አይቻልም።

3) ከላይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም በሃገር ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የከተማና የአካባቢ ስያሜዎችን በመያዝ የተመዘገቡና ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም ሳይመዘገቡ ቀደም ሲል ጥቅም ላይ የዋሉ የንግድ ምልክቶች ምዝገባ እንዳለ የሚቀጥል ይሆናል።

13) የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የንግድ ምልክት እንደገና ምዝገባ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ልማዳዊ አሰራሮችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

14. መመሪያውን ስለማሻሻል፤

ይህን መመሪያ ለማሻሻል የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና በጽ/ቤቱ የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት አብላጫ ድምጽ ሲታመንበት ሊሻሻል ይችላል፤

15. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በጽ/ቤቱ የማኔጅመንት ኮሚቴ ዓባላት አብላጫ ድምጽ ከጸደቀበት ታህሳስ 21 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ታህሳስ 21 ቀን 2006 ዓ.ም

ብርሃኑ አዴሎ

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ